የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No. …21
ADDIS ABABA 21th April, 2026

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፩/፪ሺ፲፰ ዓ.ም
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ አዋጅ……
……ገጽ፲፱ሺ፮፻፴፯

Content

Proclamation No. 1401/2026
Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation on Payment for Ecosystem Services……..…….....Page 19637

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፩/፪ሺ፲፰ ዓ.ም

የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ አዋጅ

ኢትዮጵያ ብዝሃነት ባላቸው ሥርዓተ ምህዳሮች የበለፀገች እና እነዚህ ሥርዓተ ምህዳሮች በሀገራዊ የልማት ጥረቶች ላይ ያላቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ አስተዋፅኦ ማሳደግ በማስፈለጉ፤

እነዚህ ሥርዓተ-ምህዳሮች ዘላቂ ባልሆነ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ምክንያት በከፍተኛ ጫና ውስጥ በመሆናቸው ሥርዓተ ምህዳርን በዘላቂነት ለማስተዳደር የሚያስችል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የፌደራል እና የክልል ተቋማት፣ የግሉ ዘርፍ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ልዩ ፍላጎት እና ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የአሰራር ሥርዓቶችን መዘርጋት በማስፈለጉ፤

PROCLAMATION No. 1401/2026

PROCLAMATION ON PAYMENT FOR ECOSYSTEM SERVICES

WHEREAS, Ethiopia is endowed with diverse ecosystems and it is necessary to enhance the socio-economic and environmental contributions of these multiple ecosystems to the overall national development endeavors;

WHEREAS, these ecosystems are under high pressure due to the unsustainable use of natural resources and it has become necessary to develop a legal framework for payment of ecosystem services to promote practices that guarantee sustainable ecosystem management

WHEREAS, it is necessary to establish operational systems of payments for ecosystem services that take into account the specific interests and conditions of federal and regional institutions, the private sector, and non-governmental organizations;

በመሆኑም በኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀፅ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና አንቀፅ ፶፩ ንዑስ አንቀፅ (፭) ላይ የተቀመጠውን መሰረት አድርጎ ይህ አዋጅ ታውጇል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ አዋጅ ቁጥር ፩፹፬፻፩/፪፹፬፲፰ ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"ሥርዓተ ምህዳር"** ማለት ዕፅዋት ፣እንስሳትና በዓይን የማይታዩ ደቂቅ አካላት በአካባቢያቸው ካለ ሕይወት ከሌላቸው እንደ አየር፣ አፈርና ውሀ ጋር ያላቸው ተለዋዋጭ እና ውስብስብ መስተጋብር ነው፤

፪/ **"የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት"** ማለት ሥርዓተ ምህዳር ለሰው ልጆች እና ለኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ነው፤

፫/ **"የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ"** ማለት አንድ የተወሰነ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚዎች አንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢዎች ሲገዛ እና አቅራቢው አገልግሎቱን በዘላቂነት የሚያቀርብበት በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ የሚከናወን ግብይት ነው፤

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and Article 51 Sub-Article (5) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby Proclaimed as follows.

PART ONE
GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Proclamation may be cited as 'Payment for Ecosystem Services Proclamation No 1401/2026.

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ **"Ecosystem"** means a dynamic complex of plant, animal and micro-organism communities and their non-living environment such as air, soil and water interacting as a functional unit;

2/ **"Ecosystem Service"** means the contribution that an ecosystem provides to human beings and to the economy;

3/ **"Payment for Ecosystem Service"** means a voluntary transaction in which a well-defined ecosystem service likely to secure that services is bought by at least one ecosystem service beneficiary from one or more ecosystem service provider if and only if the ecosystem service provider continues to supply that service;

፬/ "ጥቅል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት" ማለት ከአንድ በላይ የሆነ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅርቦት ላይ ትኩረት ያደረገ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ነው፤

4/ "Package of Ecosystem Service" means a payment for ecosystem service agreement that focuses on the supply of more than one ecosystem service;

፭/ "የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ" ማለት የሥርዓተ ምህዳር አግልጋሎቱ ተጠቃሚ የሆነ እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት እንዲያድግ ወይም እንዲያገግም ላደረገው የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው፤

5/ "Ecosystem Service Beneficiary" means beneficiaries of ecosystem services who are willing to pay an ecosystem Service provider for ecosystem services that safeguard, enhance or restore;

፮/ "የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ" ማለት ከመሬት ወይም ከተፈጥሮ ሀብት ጋር በተያያዘ ባለመብት የሆነ እና ከሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ ክፍያ የሚቀበል ሰው ነው፤

6/ "Ecosystem Service Provider" means a person who has rights related to land or natural resources and who receives payment from the ecosystem service beneficiary;

፯/ "አረጋጋጭ" ማለት በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ስምምነት ውስጥ የሚጠበቁ ውጤቶች መገኘታቸውን የሚያረጋግጥ ባለሥልጣኑ ወይም በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

7/ "Verifier" means the authority, or any person authorized by it, that confirms the delivery of the expected results under a payment for ecosystem services agreement;

፰/ "አደራዳሪ" ማለት በአገልግሎት አቅራቢ እና በአገልግሎት ተጠቃሚ መካከል የሚደረግ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ስምምነት ላይ መሠያዊ ድጋፍ እንዲሰጥ በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

8/ "Intermediary" means a person authorized by the Authority to provide professional support in an ecosystem services agreement made between the ecosystem service provider and the ecosystem service beneficiary;

፱/ "የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት መነሻ ልኬት" ማለት የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት በሌለበት ሁኔታ ከአንድ ሥርዓተ ምህዳር ሲገኝ የነበረ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት የሚገኝበት ደረጃ ነው፤

9/ "Ecosystem Service Measurement Baseline" means the level of ecosystem service provision in the absence of the payment for ecosystem service agreement;

፲/ **"የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጨማሪነት"** ማለት የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ከመፈፀሙ አስቀድሞ ከነበረ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት መነሻ ልኬት ላይ የጨመረ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ማሻሻያ ነው፤

10/ **"Additionality"** means any improvement above the ecosystem service measurement baseline that is additional to the scenario that would have occurred in the absence of the payment for ecosystem service agreement;

፲፩/ **"ቅድመ ሁኔታ"** ማለት ከ አንድ ሥርዓተ ምህዳር ሊገኝ የታቀደው የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ውጤት ማስገኘቱ የሚረጋገጥበትና ክፍያ ለመክፈል የሚያስችል መስፈርት ነው፤

11/ **"Conditionality"** means a performance criterion upon which payment is provided upon condition that the provision of the ecosystem service has been delivered;

፲፪/ **"አሉታዊ ተፅዕኖ"** ማለት ከሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ከሚፈፀምበት መልክዓ ምድራዊ ክልል ውስጥም ሆነ ውጭ በስምምነቱ አፈፃፀም ምክንያት የሚከሰት ተፅዕኖ ነው፤

12/ **"Negative Impact**" means an impact that occurs either within or outside the geographical area where the payment for ecosystem services agreement is implemented, as a result of the execution of that agreement;

፲፫/ **"ዘላቂነት"** ማለት የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ስምምነት በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅርቦት ላይ የሚኖረው ማሻሻያ ሲሆን ከስምምነቱ ዘመን በላይ የሚኖር ማሻሻያን የሚጨምር ነው፤

13/ **"Permanence"** means the ability of a payment for ecosystem service agreement to achieve long-term improvements to ecosystem services supply including those that persist beyond the period of the payments;

፲፬/ **"ውጤት ተኮር ክፍያ"** ማለት በተረጋገጠ የሥርዓተ ምህዳር አቅርቦት መሰረት የሚፈፀም ክፍያ ነው፤

14/ **Performance-Based Payments"** means payment made based on the actual supply of ecosystem services;

፲፭/ **"ግብዓትን መሰረት ያደረገ ክፍያ"** ማለት የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅርቦት ለመጨመር በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ውል ላይ የተቀመጡ ውጤቶችን ሊያስገኙ ለሚችሉ ተግባራት የሚፈፀም ቅድመ ክፍያ ነው፤

15/ "**Input-based Payment**" means an advance payment made for activities that can generate the results set out in a payment for ecosystem services contract in order to increase the provision of ecosystem services;

፲፮/ **"የተረጋገጠ ውጤት"** ማለት የተለካ፣ ክትትል የተደረገበት እና በገለልተኛ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ውጤት ነው፤

፲፯/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀፅ ፵፯ መሰረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፰/ **"ባለሥልጣን"** ማለት የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤

፲፱/ **"የክልል ባለሥልጣን"** ማለት ማንኛውም በክልል ደረጃ ያለ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ለማስተዳደር ዓላፊነት የተሰጠው ተቋም ነው፤

፳/ **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፩/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይገልፃል፡፡

16/ **"Verified Result''** means an ecosystem service outcome that has been measured, monitored, and validated by an independent verifier;

17/ **"Region''** means any Region established according to Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and, includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

18/ **"Authority''** means the Federal Environmental Protection Authority;

19/ **"Regional Authority''** means any institution mandated to administer payment for ecosystem services at the Regional level;

20/ **"Person"** means any natural or juridical person;

21/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት አቅራቢዎች፣ በሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚዎች፣ አደራዳሪዎች እና በዚህ አዋጅ አባሪ ፩ ስር በተዘረዘሩት የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ዓይነቶች ላይ በሁሉም የኢትዮጵያ ግዛት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall apply uniformly in the territory of Ethiopia on ecosystem service providers, ecosystem service beneficiaries, intermediaries and to the ecosystem services listed under Annex I of this Proclamation.

ክፍል ሁለት
የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ መርሆዎች እና መልክዓ-ምድራዊ ሽፋን

፬. የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ መርሆዎች

ማንኛውም የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መርሆዎች መከተል ይኖርበታል ፡-

1/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ እና የአገልግሎት አቅራቢ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ዋጋ ስምምነትን በፍቃደኝነት የሚገቡ መሆኑ፤

2/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ ክፍያውን በቀጥታ ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ የሚከፍል መሆኑ፤

3/ ክፍያ የሚፈፀመው አንድ የተወሰነ ሥርዓተ-ምህዳር ሁኔታን የማሻሻል፣ የመጠበቅ ዓላማ ለሚያደርጉ የመሬት፣ የውሃና ሌሎች ሀብቶች አያያዝ ሥርዓቶች መሆኑ፤ እና

4/ በአንድ አካባቢ ከሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ የመሆን ሂደት በሌላ አካባቢ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያስከትል መሆኑ።

፭. የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ መልክዓ-ምድራዊ ሽፋን

፩ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መልክዓ- ምድራዊ ሽፋን መሰረት ሊሆን ይችላል፡-

ሀ) ዓለም አቀፍ

ለ) ሀገር አቀፍ

ሐ) ክልል አቀፍ

መ) ተፋሰስ ወይም ንዑስ ተፋሰስ

ሰ) ወረዳ

PART TWO
PRINCIPLES OF PAYMENT FOR ECOSYSTEM SERCIVES AND GEOGRAPHIC COVEREGE

4. Principles of Payment for Ecosystem Service

Any payment for ecosystem services must follow the principles listed below:

1/ The ecosystem service beneficiary and the ecosystem service Provider enter in to agreement for payment of ecosystem service on a voluntary basis;

2/ Payments shall be made by the ecosystem service beneficiary directly to the ecosystem service provider;

3/ Payments shall be made for land, water and other natural resource management practices that aim to improve the extent or condition of particular ecosystem to increase the supply of ecosystem services;

4/ Securing an ecosystem service in one location shall not lead to negative impact elsewhere.

5. Geographic Coverage for Payment of Ecosystem Service

1/ The following spatial scales may be considered for payment for ecosystem service agreement;

a) International

b) National

c) Regional

d) Basin or Sub- Basin

e) Local level

ክፍል ሦስት

ጥቅል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ይዘት

፮. ጥቅል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት

፩. የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ቢያንስ አንድ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ዓላማ ማድረግ አለበት፡፡

፪. የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ጥቅል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ዓይነቶችን ታሳቢ ሊያደርግ ይችላል፡-

ሀ) አንድ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ ከአንድ ሥርዓተ ምህዳር የሚገኙ ሙሉ አገልግሎቶችን ለማግኘት ክፍያ ሲፈፀም፤

ለ) ከአንድ በላይ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚዎች ከአንድ ሥርዓተ ምህዳር የሚገኙ አገልግሎቶችን ለማግኘት በተናጠል ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢዎች ክፍያ ሲፈፅሙ፤

ሐ) ከአንድ ሥርዓተ ምህዳር የሚገኙ አንድ ወይም የተወሰኑ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚሸጥ ሲሆን ሌሎች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ያለ ክፍያ በነፃ ሲቀርቡ ነው፡፡

PART THREE

PACKAGE OF ECO SYSTEM SERVICE AND CONTENT OF AGREMENT ON ECOSYSTEM SERVICE PAYMENT

6. Package of Ecosystem Services

1/ A payment for Ecosystem service agreement shall focus on at least one ecosystem service.

2/ A Payment for Ecosystem Services agreement may take into consideration the following types of ecosystem service packages:

a) When a single ecosystem service beneficiary pays for the full package of ecosystem services that arise from the same ecosystem;

b) When multiple ecosystem service b eneficiaries pay separately for the ecosystem service providers for the ecosystem services that arise from the same ecosystem;

c) One or more specific ecosystem services from a single ecosystem are sold to ecosystem service beneficiary, while other ecosystem services are provided free of charge.

፯. <u>የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ይዘት</u>

፩. ማንኛውም የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ይዘት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ) የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ አድራሻና ሙሉ መረጃ፤

ለ) የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ መብትና ግዴታዎች፣ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የተሸጡበት የቦታው ባለቤትነት ሲለወጥ እና በመጀመሪያ ዋና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ እና በማንኛውም ቀጣይ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚዎች የስርዓተ ምህዳር አገልግሎቱ እንደገና ሲሸጥ ያሉ ድንገተኛ ሁኔታዎች መካተት አለበት፤

ሐ) ስምምነቱ የሚፈፀምበት ቦታ ዝርዝር ሁኔታ፤

መ) የክፍያ አይነት፣ የአከፋፈል ሁኔታ እና ክፍያ ጊዜ፤

ሰ) የክትትል፣ የማረጋገጫ እና የሪፖርት መስፈርቶች ፤

ሸ) በስምምነቱ የተጠቀሱ ግዴታዎችን ያለማክበር ውጤቶች፤

ቀ) ስምምነት ስለሚሻሻልበት ሁኔታ፤

በ) ስምምነቱ ስለሚሰረዝባቸው ሁኔታዎች፤

7. <u>Contents of a Contractual Agreement for Payment for Ecosystem Service</u>

1/ The content of any contractual agreement for payment for ecosystem service shall contain the following components:

a) Details and addresses of the ecosystem service beneficiary and the ecosystem service provider;

b) Rights and responsibilities of the ecosystem service beneficiary and the ecosystem service provider, including contingencies for the change of ownership of the areas from which the ecosystem services sold and the re-sale of ecosystem services by the first original and any subsequent ecosystem service ben eficiary;

c) A detailed description of the location where the agreement will be implemented;

d) The type of payment, the payment arrangement method and the payment time.

e) Monitoring, verification and reporting requirements;

f) The consequences of failing to comply with the obligations specified in the agreement;

g) The conditions under which the agreement may be amended.

h) The conditions under which the agreement may be canceled;

ተ) የስምምነቱ ዘመን፤

ቸ) ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች በሚደርሱ ጉዳቶች ምክንያት የሚደርስ ኪሳራን የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ የሚጋሩበት ሁኔታ፤

ነ) የግጭት አፈታት ዘዴ፤ እና

ኘ) የተዋዋይ ወገኖች ፊርማ።

ክፍል አራት

የአከፋፈል ሁኔታ፣ የፋይናንስ ምንጭ እና የጥቅም መጋራት

፰. የአከፋፈል ሁኔታ

፩/ ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚዎችና በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢውች ስምምነት የሚወሰን ሲሆን አደራዳሪ የአከፋፈል ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይችላል።

፪/ በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት መሰረት ክፍያ ተፈፃሚ የሚሆነው ለተረጋገጡ ውጤቶች ብቻ ነው።

፫/ ውጤት ተኮር ወይም ግብዓትን መሰረት ያደረገ ክፍያ ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ሊውል ይችላል።

፱. የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት የፋይናንስ ምንጭ

፩/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የገንዘብ ምንጮች ከዚህ በታች ከተዘረዘሩ ምንጮች ሊሆን ይችላል፦

ሀ) መንግስት ህዝብን በመወከል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎትን ለማሳደግ፣ መንግስት ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ የሚከፍልባቸው የመንግስት ክፍያ መርሃ ግብሮች፤

i) duration of the contract;

j) Circumstances in which the service beneficiary and service provider may share the compensation resulting from damages caused by reasons beyond their control ;

k) Dispute resolution methods;

l) Signature of each party.

PART FOUR

MODE OF PAYMENT, FINANCIAL SOURCE AND BENEFIT SHARING

8. Mode of payment

1/ The payment made for an ecosystem service shall be the result of a negotiation between the ecosystem service beneficiary and the ecosystem service provider, which may be facilitated by an intermediary.

2/ The payment for ecosystem service shall take effect only when verifiable esults are delivered as per the agreement.

3/ Input-based and performance-based payments may be used for payment for ecosystem service.

9. Financial source of ecosystem services

1/ Payment for ecosystem services may be financed from one of the following sources:

a) Public payment schemes through which the government pays an ecosystem service provider to enhance ecosystem services on behalf of the public;

ለ) ግለሰቦች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ለማግኘት በቀጥታ ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ ክፍያ የሚፈፅሙበት፤ እና

ሐ) በመንግስትና በግለሰብ ጥምረት የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ለማግኘት የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ ክፍያ የሚፈፀምበት ነው።

፲. የጥቅም መጋራት

፩/ ማንኛውም የጥቅም መጋራት ስምምነቶች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ እና በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ መካከል ከመፈረሙ አስቀድሞ መከናወን አለበት።

፪/ በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢዎች መካከል የሚደረግ የጥቅም መጋራት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

ሀ) የጥቅም መጋራት ሂደቱ ውጤት ያስገኙ አካላትን የሚያበረታታ እና ዝቅተኛ አስተዋፅኦ ላላቸው በተመሳሳይ ዝቅተኛ ጥቅም የሚያስገኝ መሆን አለበት፤

ለ) ግልፅና ከአድሎ የፀዳ መሆኑ በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢዎች፣ በባለሥልጣኑ እና የክልል ባለሥልጣን መወሰን አለበት።

ሐ) የጥቅም መጋራት ሥርዓቱ በተቻለ መጠን የህብረተሰብ መሰረት ባላቸው ህብረተሰቡን በውሳኔ ሰጪነት የሚያሳትፍ የሥርዓተ-ምህዳር ልማት እና ጥበቃ ማህበራት መቋቋም አለበት።

b) Payment in which individuals make direct payments to ecosystem service providers in order to obtain ecosystem services;

c) Public private payment schemes that draw on both government and private funds to pay an ecosystem service provider for the delivery of ecosystem services.

10. Benefit Sharing

1/ Any benefit sharing arrangements between the ecosystem servicebe neficiary and the ecosystem ervice provider shall be agreed prior to the implementation of the payment for ecosystem service agreement.

2/ Any benefit sharing arrangement of payment for ecosystem service agreement Service beneficiary and Service provider shall consider the following issues:

a) The arrangement shall reward actual behaviour and provide a significant disincentive for poor performance to create ownership and responsibility for good performance;

b) the ecosystem service providers, the Authority and Regional Authorities shall ascertain the process is transparent and equitable;

c) The benefit-sharing system shall be established through community-based ecosystem development and conservation associations that involve the community in decision-making.

፫/ ባለሥልጣኑ በሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የጥቅም መጋራት ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣት አለበት፡፡

3/ A Directive on benefit-sharing arrangements for payment for ecosystem service agreements shall be issued by the Authority.

ክፍል አምስት
የአደራዳሪ ሚና እና የአገልግሎት አቅራቢ ሚና

PART FIVE
ROLE OF THE INTERMEDIARY AND SERVICE PROVIDER

፲፩. የአደራዳሪ ሚና

11. Role of the Intermediary

፩/ አደራዳሪ በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ላይ ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢዎች እና ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ጉዳዮች ላይ የሙያ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡-

1/ The intermediary may provide technical support to the ecosystem service beneficiary and the ecosystem service provider in the following potential roles under a payment for ecosystem services agreement:

ሀ) የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ዋጋ ትመና ላይ እና ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢዎች እና ለሥርዓተ ምህዳርአገልግሎት ተጠቃሚዎች የሙያ ድጋፍ ማድረግ፤

a) Provide professional support to ecosystem service providers and ecosystem service beneficiaries on the valuation of ecosystem services;

ለ) የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ ማስተዋወቅና እና በመካከላቸው መልካም ግንኙነት እንዲኖር የሙያ ድጋፍ ማድረግ፤

b) Introducing ecosystem service beneficiary and ecosystem service provider and building harmonious relationship between them;

ሐ) የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት መነሻ ልኬት እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጨማሪነት ወሰን ጥናት ላይ የሙያ ድጋፍ ማድረግ፤

c) Providing technical support in studies on baseline measurement of ecosystem services and the assessment of additionality limits of ecosystem services;

መ) ዋጋዎችን ለመወሰን ፣ የገንዘብ ድጎማዎችን ለማግኘት፣ ስምምነቶችን በማዘጋጀት እና በጋራ ተቀባይነት ባለው የክፍያ ሥርዓት ላይ ማስማማት፤

d) Determining prices, obtaining financial subsidies, preparing agreements, and reaching consensus on a mutually accepted payment system;

ሠ) በክትትል፣ በሪፖርት እና በማረጋገጥ ላይ የሙያ ድጋፍ ማድረግ።

፪/ አደራዳሪ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ፈቃድ የተሰጠው እና የተመዘገበ መሆን አለበት።

፲፪. <u>ክትትል ፣ሪፖርት እና ማረጋገጥ</u>

፩/ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት አተገባበር በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ ክትትል እየተደረገበት ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚው እና ለባለሥልጣኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ለማረጋገጥ ሪፖርት ይላካል፡-

ሀ) ከሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት የሚጠበቁ ውጤቶች እየተገኙ መሆኑን፤

ለ) ክፍያ ግብዓትን መሰረት ያደረገ ከሆነ ግብዓቱ የሥርዓተ ምህዳሩን ሁኔታ በእርግጥ እያሻሻለ መሆኑን፤

ሐ) በስምምነቱ ከተሸፈነው አካባቢ ውጭ የሥነ-ምህዳሩን ሁኔታ ወይም የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የማያሳድር መሆኑን፤

መ) አግባብነት ያላቸው የቁጥጥር መስፈርቶች የተከበሩ መሆኑን።

፪/ በሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት መሰረት ተጨማሪ አገልግሎት እየተገኘ መሆኑን ክትትል ለማድረግ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቱ መነሻ መወሰን አለበት።

e) Providing technical support in monitoring, reporting, and verification.

2/ The intermediary shall be registered and approved in accordance with a directive issued by the Authority.

12. <u>Monitoring, Reporting and Verification</u>

1/ The implementation of a payment for ecosystem service agreement shall be monitored by the ecosystem service provider and reported to the ecosystem service beneficiary and the Authority to ensure the following issues:

a) The expected results from the payment for ecosystem service agreement are being delivered;

b) If the payment is performance-based, the payment should clearly reflect that it is improving the state of the ecosystem;

c) The agreement shall ensure that there is no negative impact on the ecosystem condition or the provision of ecosystem services outside the area covered by the agreement;

d) Relevant regulatory requirements are being complied with.

2/ A payment for ecosystem service agreement shall define the ecosystem service measurement baseline that facilitates accurate monitoring which indicate the level of additionality being delivered.

፫/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት መሰረት በስምምነቱ ምክንያት አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያደርስ የሚችልባቸውን አካባቢ መለየት አለበት፡፡

፬/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢን የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት አተገባበርን የመከታተልና ሪፖርት የማቅረብ ዓላፊነት በባለሥልጣኑ ሲፈቀድ ለህዝባዊ ተቋም ወይም ለአደራዳሪ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

፭/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት አተገባበር በየጊዜው በባለሥልጣኑ ፍቃድ በተሰጠው አረጋጋጭ መረጋገጥ አለበት፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ የአረጋጋጮች የሙያ ብቃት ፍቃድ ለስመጠት የሚያስችል መመሪያ ማውጣት አለበት፡፡

ክፍል ስድስት
የባለሥልጣኑ ኃላፊነት

፲፫. የባለሥልጣኑ ኃላፊነት

፩/ ባለሥልጣኑ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

ሀ) ለተለያዩ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት የሚውሉ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት መነሻ ልኬት መወሰኛ እና የክትትል፣ የሪፖርት እና የማረጋገጫ የቴክኒክ መመሪያዎች ያዘጋጃል፤

ለ) የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት እና ተያያዥ የክትትል ሪፖርቶች የሚቀመጡበት መዝገብ ያደራጃል፤

3/ A payment for ecosystem service agreement shall define the areas potentially affected as a result of the ecosystem service agreement.

4/ The ecosystem service provider responsibility to monitor and report on the implementation of the payment for ecosystem service agreement may be transferred to a public institution or an intermediary approved by the Authority.

5 The implementation of a payment for ecosystem service agreement shall be periodically verified by and independent verifier authorized by the Authority.

6/ The Authority shall issue a Directive for the issuance of competence certificates to verifiers.

PART SIX
RESPONSIBILITIES OF THE AUTHORITY

13. Responsibilities of the Authority

1/ The Authority shall have the following responsibilities in relation to Payment for Ecosystem Services:

a) Develop technical guidelines on how to develop ecosystem service measurement baselines for various types of payment for ecosystem service agreements and for determining the areas potentially adversely affected by ecosystem service agreement;

b) Keep a public register of ecosystem service agreements and related monitoring reports;

ሐ) የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት የክትትል ሪፖርቶችን በመገምገም የጥራት ማረጋገጫ ያከናውናል፤

መ) ለአደራዳሪዎች ፍቃድ ይሰጣል፣ ፍቃድ የተሰጣቸው የአደራዳሪዎች ዝርዝር የያዘ መዝገብ ያደራጃል።

c) Carry out quality assurance by reviewing monitoring reports of payment for ecosystem service agreement;

d) Approve intermediaries and maintain a public register of approved intermediaries.

፲፬. <u>የክልል ኃላፊነት</u>

ክልሎች ይህን አዋጅ መነሻ በማድረግ በክልሉ ተፈጻሚ የሚሆኑ የህግ ማዕቀፎችን ያወጣሉ።

14. <u>Responsibilities of Regions</u>

Regional States shall issue legal frameworks applicable in their Region based on this Proclamation.

<u>ክፍል ሰባት</u>
<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

<u>PART SEVEN</u>
<u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

፲፭. <u>ግዴታን አለማክበር</u>

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ ላይ የተቀመጡ ግዴታዎች ያልተከበሩ እንደሆነ ወይም ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ምክንያቶች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነትን መሰረዝ ይችላል፦

ሀ) በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ፣ በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ፣ አደራዳሪ ወይም አረጋጋጭ ሆን ተብሎ ሀሰተኛ መረጃ ቀርቦ ከነበረ፤

ለ) የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢው በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ስምምነት ላይ የተመላከቱ የውጤት ማመላከቻ መስፈርቶችን በተደጋጋሚ ማሳካት ካልቻለ፤

ሐ) የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢው በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ስምምነት በተቀመጠ የጊዜ ሰሌዳ የክትትል ሪፖርት መላክ ካልቻለ፤

15. <u>Non-Compliance</u>

1/ In the event of non-compliance with the procedures established under this Proclamation, the Authority shall have the power to cancel agreements in any of the following circumstances:

a) Intentional submission of false information by the ecosystem service provider, ecosystem service beneficiary, intermediary, or verifier;

b) Consistent failure by the ecosystem service provider to achieve the performance indicators specified in the payment for ecosystem services agreement;

c) If the ecosystem service provider fails to submit the monitoring report according to the schedule set in the payment for ecosystem service agreement;

መ) በስራ ላይ ያሉ የአካባቢ ሕግ ጥሰቶች ሲፈፀም፤

ሠ) የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ ከሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ስምምነት የሚገኝ ክፍያን ላልተፈቀደ ዓላማ ሲያውል፤

ረ) የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ስምምነቱ ከተዋዋይ ወገኖች ውጭ በሆኑ ምክንያቶች መቀጠል የማይችል ከሆነ፤

ሸ) የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢዎች የጥቅም መጋራት እቅድ በአግባቡ ሳይተገበር ሲቀር፡፡

፪/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅራቢ ከአቅም በላይ የሆኑና ሊወገዱ የማይችሉ ችግሮች እንደ በተባይ መወረር ፤ የዝናብ ሁኔታ መለዋወጥና የተፈጥሮ የእሳት አደጋ ያሉ ክስተቶች ምክንያት ጉዳት ሲከሰት ችግሮችን የሚጋሩበት ሁኔታዎች ላይ መስማማት ይኖርባቸዋል፡፡

፲፮. በስራ ላይ የሚገኙ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነቶች

፩/ ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፕሮጀክቶች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ላይ እድሳት ወይም ማሻሻል የሚፈፀመው በዚህ አዋጅ መሰረት መሆን አለበት፡፡

d) violation of applicable environmental laws;

e) If the ecosystem service provider use the payment for ecosystem service agreement for an unauthorized purpose;

f) If the payment for ecosystem services agreement cannot be continued for reasons beyond the control of the parties;

g) Failure by the ecosystem service provider to implement the benefit-sharing plan as required under the agreement.

2/ The ecosystem service beneficiary and the ecosystem service provider shall agree how risks of unavoidable non-compliance will be shared due to an event which is beyod their control such as through insect infestaions, shifts in rainfall patterns, wildfire.

16. Ongoing Payment For Ecosystem Service Agreement

1/ This Proclamation shall not apply to any payment for ecosystem service agreement related to projects initiated before this Proclamation comes into effect.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, any renewal or amendment of a payment for ecosystem agreement shall be in accordance with this Proclamation.

፲፮. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለአዋጁ አፈጻጸም የሚረዱ ደንቦች ሊያውጣ ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ለአዋጁ አፈፃፀም የሚያግዙ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፯. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ቀን ፲፫ ሚያዝያ ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

ታዬ አጽቀሥላሴ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

17. <u>Powerto Issue Regulations and Directives</u>

1) The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the proper implementation of this Proclamation.

2) The Authority may issue Directives to assist in the implementation of this Proclamation.

18. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall come into force upon Publication on the Federal Negarit Gazettee.

Done at Addis Ababa, on this Day of 21 April 2026.

TAYE ASTKE SELASSIE
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA